# ማገልገል የህሊና እርካታም የዜግነት ግዴታም ነው፡፡

ጳጉሜን ለኢትዮጵያን በሚል መሪ ቃል ጳጉሜ 1 የአገልጋይነት ቀን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በቢሮው ክራተኛው፣ከአመራሩና ከተገልጋዮች ጋር ጳጉሜ 1/2015 ዓ.ም በድምቀት አክብሯል፡፡

አዲስ አበባ፣ ጳጉሜ 01/13/2015 ዓ.ም፤ ጳጉሜን_ለኢትዮጵያ! በሚል መሪ ቃል የጳጉሜ 6 ቀናት በልዩ ልዩ ሁነትና መልዕክት የሚከበር ሲሆን ዛሬ የአገልጋይነት ቀን የኮሚሽኑ አመራሮች፣ሰራተኞችና ባለጉዳዮች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ፣ ዋና ኦዲተር፣ማህበራዊ ፍርድ ቤት እና የከተማቦታና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመራሮችና ሰራተኞች በተገኙበትና የባህል አልባሳት በመልበስ በማለዳው የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በመዘመርና ሰንደቅ ዓላማ በመስቀል በድምቀት ተጀምሯል።

በፕሮግራሙ ማስጀመሪያ መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ሀላፊ አቶ ተክሌ በዛብህ እንኳን አደረሳችሁ በማለት አገልጋይነት ከሁሉም በላይ ለራስ እርካታ የሚገኝበት የቅንነት እና የሀገር ወዳድነት መገለጫ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዝዳንት አቶ ታረቀኝ አሰፋው እንደገለፁት ማገልገል የህሊና እርካታም የዜግነት ግዴታም ነው! የቢሮአችን ሰራተኞች በቅንነት፣በታማኝነትና በፍቅር ለምትሰጡት አገልግሎት ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በአዲሱ ዓመትም በላቀ ተነሳሽነት የአገልግሎት አሰጣጣችን እናስቀጥላለን ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ በኃይሉ ክብረት በበኩላቸው ማገልገል የህሌና እርካታ ነው፡፡ማገልገል በስራ ብቻ አይደለም በመንፈሳዊ አለምም ያለ ነው፡፡ ስለዚህ ሁላችሁም ለምትሰጡት አገልግሎት እያመሰገንኩ አዲሱ ዓመት የሰላምና የደስታ እንዲሆንላችሁ እመኛለው በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በመጨረሻም የቀጣይ የጳጉሜ ቀናት በድምቀት እንዲከበሩ አቅጣጫ በመስጠትና የፎቶ ፕሮግራም በማከናወን የአገልግሎት ቀን ሲከበር ውሏል፡፡




ጳጉሜ 1 የአገልጋይነት ቀን
መልካም አዲስ ዓመት
TECNO
SPARK


MANA MURTII OL'IYYANNOO
MAGAALAA FINFINNEE